

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የሄልሲንኪ ደብረ አሚን አቡነ ተክለ ሃይማኖት

ቤተ ክርስቲያን፣ ፊንላንድ

የመዝሙርና ሥነ-ፅሑፍ ንዑስ ክፍል



መዝሙራት ለግንቦት 13 ቀን 2008 ዓ.ም

1. አልቦ እምቅድሜሁ

አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ እምድሬሁ ውዕቱ ማህሌታይ ሰብእ ዘከማሁ /፪/

ያሬድ ካህን ይኬልህ ትንሣኤሁ ኢየዓዱ እንስሳ ወሰብእ እምን ሠላስ ዜማሁ/፪/

ከእርሱም በፊት ከእርሱም በኋላ እንደእርሱ ማኅሌታዊ ሰው የለም /፪/

ያሬድ ካህን ትንሣኤውን ይናገራል ሰው ወይም እንስሳ ከሦስቱ ዜማዎቹ አይወጣም /፪/

2. አማን በአማን

አማን በአማን (፪) ተክለ ሃይማኖት

ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ (፪)

3. ተክለ ሃይማኖት

ተክለ ሃይማኖት የአምላክ ባለሟል ፍጹም ናቸው (፪)

ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው ያበራል ይኸው (፪)

4. ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ

ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ መጠነ በዝኃ ሕማሙ (፪)

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ (፪)

እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍልሰተ ሥጋሁ ወአፅሙ (፪)

አዝ...

እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለዓለት በስሙ (፪)

አዝ...

ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ(፪)

አዝ...

ትርጉም፦ ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ብዙ ሕማም የተቀበለባት የሥጋውና የአፅሙ ፍልሰት የተደረገባት በስሙ ከተሰየሙ አድባራት በላይ የሆነች ኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የቀደሳት ደብረ ሊባኖስ ተክለ ሃይማኖትን ታመሰግናሰች

### 5. አባ አቡነ

አባ አቡነ (፪) መምህርነ አባ ተክለ ሃይማኖት (፪)

እምአእላፍ ኅሩይ (፪) አባ (፫) አቡነ ተክለ ሃይማኖት (፪)

ትርጉም፡- መምህራችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከብዙዎቹ መካከል የተመረጥክ ነህ

### ወረብ

አሐዱ ማኅበሮሙ ክርስቶስ ሠምራ ወተክለ ሃይማኖት

በእንተ መስቀሉ ለክርስቶስ አሐደ መሬተ ኮኑ

መዝሙር

በእንተ መስቀሉ (፬)

ኸኸ ለክርስቶስ (፫) በእንተ መስቀሉ

### 6. ኵሎ ዘፈቀደ

ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር (፪)

በሰማይኒ ወበምድረኒ ወበባሕርኒ ወበኵሉ <u>ቀላያት</u> (፬)

ትርጉም፡- እግዚአብሔር በሰማይና በምድር በባሕርም በፈሳሾችም የወደደውን አደረገ

### 7. አምላክ አለ መሃላችን

ደስ ይበለን /፪/ አምላክ አለ መሃላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ

ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን እድሜ የጨመረልን
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን

አዝ፣

ኃጢአትህን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የጽድቅ ሕይወት

አዝ፣

ድንግልማርያም ትጸልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንዴ ቢያድለን

አዝ፣

እልል በሉ የኀበኛችሁ
በቸርነት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ







### 8. ጽላት ዘሙሴ ጽላት

ጽላት ዘሙሴ ጽላት (፬) ማርያም ቅድስት (፪)

ሙሴ ከፈጠሪ የተቀበላት አሠርቱ ትዕዛዛት የተጻፈባት ጽላት ዘሙሴ ጽላት (፪)

ይዕቲ ዕፀ መድኃኒት (፬) ማርያም ቅድስት (፪)

### 9. ጽላት ዘሙሴ

ጽላት ዘሙሴ እፀ ጳጦስ ዘሲና (፪)

ጸናጽል (፫) ለአሮን ካህን (፪)

### 10. ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም

እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒአለም (፪)

| | | |
|---|---|---|
| ንፅህት ስለሆንሽ | እመቤቴ | እመቤቴ |
| እንከን የሌለብሽ | ›› | ›› |
| የፍጥረታት ጌታ | ›› | ›› |
| ባንቺ ያደረብሽ | ›› | ›› |
| የድንግል መመረጥ | ›› | ›› |
| ዜናው አስገረመኝ | ›› | ›› |
| እሳቱን ታቀፈች | ›› | ›› |
| የማይቻለውን | ›› | ›› |

አዝ…

| | | |
|---|---|---|
| ምርኩዜ ልበልሽ | እመቤቴ | እመቤቴ |
| ጥላ ከለላዬ | ›› | ›› |
| ጋሻዬ ነሽ አንቺ | ›› | ›› |
| ለኔ መመኪያዬ | ›› | ›› |
| ባለም እንዳልጠፋ | ›› | ›› |
| ህይወቴ መሮብኝ | ›› | ›› |
| እንደ ወይን አጣፍጪው | ›› | ›› |
| ድንግል ድረሽልኝ | ›› | ›› |

አዝ…

| | | |
|---|---|---|
| የምስራቅ ደጃፍ ነሽ | እመቤቴ | እመቤቴ |
| የሁላችን ደስታ | ›› | ›› |
| እሙ ለፀሐይ ጽድቅ | ›› | ›› |
| የሁሉ ጠበቃ | ›› | ›› |
| ድንግል የጽድቅ አክሊል | ›› | ›› |
| ድንግል የጽድቅ ሥራ | ›› | ›› |
| ድንግል መሰላል ነሽ | ›› | ›› |
| የተዋህዶ ተስፋ | ›› | ›› |







### 11. ውስቴታ ታቦት በውስቴታ

ውስቴታ ታቦት በውስቴታ ኦሪት በውስቴታ (፪)

ይኬልልዋ በወርቅ ይኬልልዋ (፪)

### 12. ታቦት በውስቴታ

ታቦት እንተ ውስቴታ ኦሪት በውስቴታ (፪)

ዉቱረ ይኬልልዋ በወርቅ (፪) ይኬልልዋ (፪)